

በ"ብርሃን ለዓለም" ዓለም አቀፍ አገልግሎት የቀረበ፡

# የገነትና የሲያል ራዕይ በ7 ኮሎምቢያውያን ወጣቶች

እነዚህ 7 ኮሎምቢያውያን ወጣቶች በጋራ በ**ኢየሱስ ክርስቶስ** ተወስደው ገነትንና ሲያልን አዩ። ይህ በገነት ስላዩት ድንቅ ውበት እና በሲያል ስላዩት አሰቃቂ ነገር የሰጡት ምስክርነት ነው።

*ይህ ትርጉም በመጣበት ቅጂ ምክንያት 6ቱን ምስክርነቶች ብቻ መዝግበናቸዋል። በመጀመሪያ በስፓኒሽ ድምጽ ቅጂ የተገኘ ሲሆን ገለጻዎች/ስዕሎቹ የምስክርነቱ ክፍል ሳይሆኑ በኋላ ላይ የተጨመሩ ናቸው።*

# ስለ ገነት ራእይ

---

## --- (1ኛ ምስክርነት፥ ኤሳው) ---

2 ቆሮንቶስ 12፡2

*ሰውን በክርስቶስ አውቃለሁ፥ በሥጋ እንደ ሆነ አላውቅም ወይም ከሥጋ ውጭ እንደ ሆነ አላውቅም፥ እግዚአብሔር ያውቃል፤ እንዲህ ያለው ሰው ከአሥራ አራት ዓመት በፊት እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ።*



በመጀመሪያው ገጠመኝ ጊዜ፥ ክፍል ውስጥ ነበርን። ከጌታ መገኘት የተነሳ ክፍሉ እንደገና በብርሃን ተሞላ። ኃይለኛ ከመሆኑ የተነሳ ክፍሉ በሙሉ በራ። ክፍሉ በክብሩ ተሞልቶ ነበር፥ በፊቱ መሆን በጣም ደስ ይላል።

ኢየሱስ እንዲህ አለን፥ "***ልጆቼ፥ አሁን መንግሥቴን አሳያችኋለው፥ ወደ ክብሬ እንሄዳለን።***" እጅ ለእጅ ተያይዘን ወደ ላይ ተነጠቅን። ወደ ታች ተመለከትሁ እናም ከገዛ ሰውነታችን ውስጥ ወጥተን እየሄድን ነበር። ከሰውነታችን ውስጥ ስንወጣ ነጫጭ እጀጠባቦችን ለበስን እናም በጣም በፍጥነት ወደ ላይ መሄድ ጀመርን።

የመንግሥተ ሰማያት መግቢያ ወደ ሆኑ ሁለት ጥንድ በሮች ደረስን። በእኛ ላይ እየሆነ ባለው ነገር በጣም ተደንቀን ነበር። ምስጋና ይግባውና፥ የ**እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ** እያንዳንዳቸው አራት ክንፎች ካሏቸው ከሁለት መላእክት ጋር ከእኛ ጋር በዚያ ነበር።

*መላእክቱ ያናግሩን ጀመር፥ ነገር ግን የሚናገሩትን ነገር አልተረዳንም። ቋንቋቸው ከእኛ በጣም የተለየ ነበር፥ እንዲሁም ከማንኛውም ምድራዊ ቋንቋ ጋር አይመሳሰልም። መላእክቱ አቀባበል እያደረጉልን ነበር እናም እነዚያን ግዙፍ በሮች ከፈቱልን። ብዙ ልዩ ልዩ ነገሮች ያሉበት አስገራሚ ቦታ አየን። ወደ ውስጥ ስንገባ፥*

ፍጹም ፍቅር ልባችንን ሞላው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አዕምሮን የሚያልፍ ሰላም እንደሚሰጠን ይናገራል። (ፊልጵስዩስ 4፡7)

*መጀመሪያ ያየሁት ነገር ዋላ (ዋልያ) ነበር፥ ስለዚህ ከጓደኞቼ አንዷን ጠየኳት፥ "ሳንድራ፥ እኔ የማየውን ነገር ነው እያየሽ ያለሽው?" ሲያልን ስናይ እንደነበረው እያለቀሰችም ሆነ እየጮኸች አልነበረም። እየሳቀች እንዲህ አለችኝ፥ "አዎ ኤሳው፥ ዋላ እያየሁ ነው!" ከዛም ሁሉም ነገር እውነት እንደሆነ አወቅሁ፥ የእውነት በመንግሥተ ሰማያት እንደሆንን። በሲያል ያየነው አሰቃቂ ነገር ሁሉ ወዲያው ተረሳ። በዚያ የእግዚአብሔርን ክብር እያጣጣምን ነበር። ዋላው ወዳለበት ቦታ ሄድን፥ ከኋላው ፈጽሞ ግዙፍ የሆነ ዛፍ ቆሟል! በገነቱ መካከል ነበር።*

*መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር በራእይ 2፡7 "**መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ። ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ።**"*

*ይህ ዛፍ የኢየሱስ ምሳሌ ነው፥ ምክንያቱም ክርስቶስ የዘላለም ሕይወት ነው። ከዛፉ ጀርባ ኩልል ያለ ውኃ ያለው ወንዝ አለ። (አማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የብርጭቆ ብሕር፤ እንግሊዝኛው ደግሞ "ክሪስታል ሲ"፥ crystal sea ይለዋል። ራእይ 4፡6) ጥርት ያለና የሚያምር ነበር፥ በምድር ፈጽሞ እንደማናውቀው ዓይነት። በዚያ ቦታ መቆየት ፈለግን። ብዙ ጊዜ ለጌታ "ጌታ ሆይ እባክህ! ከዚህ ቦታ አትውሰደኝ! ለዘላለም በዚህ መሆን እንፈልጋለን! ወደ ምድር መመለስ አንፈልግም!" አልነው። ጌታም መለሰልን፥ "**ለሚወዱኝ ሁሉ ያዘጋጀሁትን ትመሰክሩ ዘንድ መመለሳችሁ አስፈላጊ ነው፤ በቶሎ እመጣለሁ ሽልማቴም በእጄ ነው።**"*

ወንዙን እንዳየነው፥ ፈጥነን ወደ ውስጡ ገባን። በጌታ የሚያምን ሁሉ የሕይወት ውኃ ምንጭ ከሆዱ ይፈልቃል (የጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በዮሐንስ 7፡38) የሚለውን ጥቅስ አስታወስን። ወንዙ ውስጥ ያለው ውኃ በራሱ ህይወት ያለው ይመስላል፥ ስለዚህም ራሳችንን በውስጡ አሰመጥን። በውኃ ውስጥም ሆነ ውጭ በትክክል መተንፈስ እንችል ነበር። ወንዙ በጣም ጥልቅ ሲሆን በውስጡ የተለያየ ቀለም ያላቸው ዓሣዎች ይዋኙ ነበር። ውኃ ውስጥም ከውኃው ውጭም ያለው ብርሃን ተመሳሳይ ነው፥ በገነት ብርሃን ከአንድ ከሆነ ምንጭ ብቻ አይመጣም፥ ሁሉም ነገር እንዲሁ ደምቆ ያበራል። መጽሐፍ ቅዱስ **ጌታ ኢየሱስ** የከተማዋ ብርሃን እንደሆነ ይነግረናል።(ራእይ 21፡23) አንዳንድ ዓሦችን በእጃችን ከውኃ ውስጥ አወጣናቸው፤ አልሞቱም። ስለዚህም ወደ **ጌታ** ሮጠን ለምን እንደሆነ ጠየቅነው። **ጌታም** እየሳቀ በገነት ሞትም፣ ልቅሶም ሆነ ህመም ፈጽሞ እንደሌለ ነገረን።(ራእይ 21፡4)

ወንዙን ትተን ወዳገኘንባቸው ቦታዎች ሁሉ ሮጥን፥ ሁሉንም ነገር መንካትና መለማመድ ፈለግን። በገነት ባለው ነገር ሁሉ ተደንቀን ስለነበር ሁሉንም ነገር ይዘን ከእኛ ጋር ወደ ቤታችን ይዘን መመለስ ፈለግን። በቀላሉ በቃላት በበቂ ሁኔታ ሊገለጹ አይችሉም። ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ገነት ተወስዶ ሳለ፥ በመንግሥተ ሰማያት ካሉት ነገሮች ታላቅነት የተነሳ በቃላት መቼም ሊገልጻቸው የማይቻለውን ነገሮች አይቷል። (2 ቆሮንቶስ 12) አንዳንድ ያየናቸውን ነገሮች መግለጫ ምንም ዓይነት መንገድ የለንም።

ከዛም እጅግ በጣም ሰፊ የሆነ ቦታ መጣን፤ በጣም የሚገርምና የሚያምር ቦታ። ይህ ቦታ በከበሩ ድንጋዮች የተሞላ ነበር፤ ወርቅ፣ አርንጓዴ እንቁ፣ ቀይ እንቁና አልማዞች። መሬቱ በንጹህ ወርቅ የተሠራ ነበረ። ከዛም ሦስት ታላላቅ መጻሕፍት ወዳሉበት ሄድን። የመጀመሪያው በወርቅ የተሠራ መጽሐፍ ቅዱስ ነበር። በመዝሙረ ዳዊት ላይ **የእግዚአብሔር ቃል** ዘላለማዊ እንደሆነና **የእግዚአብሔር ቃል** በገነት ለዘላለም እንደሚኖር ይነግረናል። (መዝሙር 118(119)፡89) ግዙፉን መጽሐፍ ቅዱስ እያየን ነበር፤ ገፆቹ፣ ጥቅሶቹ ሁሉም ነገር በንጹህ ወርቅ የተሠራ ነበር።

ያየነው ሁለተኛው መጽሐፍ ከመጽሐፍ ቅዱሱ ይበልጣል። ተከፍቶ ነበር እናም መልአክ በውስጡ እየጻፈ ነበር። መልአኩ ምን እየጻፈ እንደሆን ለማየት ከ**ጌታ** ጋር ወደ መጽሐፉ ቀረብን። መልአኩ በምድር ላየ የሚፈጸሙትን ነገሮች ሁሉ እየጻፈ ነበር። የሆነው ነገር ሁሉ፤ ቀኑን፣ ሠዓቱን፥ ሁሉም ነገር ተመዝግቧል። ይህም የሚሆነው መጽሐፍት ተከፈቱ በምድርም ያሉ ሰዎች እንደየ ሥራቸው ተፈረደባቸው የሚለው የ**ጌታ** **ቃል** ይፈጸም ዘንድ ነው። (ራእይ 20፡12) መልአኩ በምድር ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ የሚያደርጉትን ነገር እየጻፈ ነበር፥ መልካምም ሆነ ክፉ፥ እንደተጻፈው።

ሦስተኛው መጽሐፍ ወዳለበት ቦታ ቀጠልን። ይሄ ደግሞ ከሁለተኛው መጽሐፍ የበለጠ ትልቅ ነው! መጽሐፉ ዝግ ነበር፥ ነገር ግን ወደ እርሱ ቀረብን። ሰባታችንም በአንድ ላይ መጽሐፉን ከማስቀመጫው አወረድነው፥ እንደጌታ ትእዛዝ፥ ከዛም በአትሮነስ(ፒላር) ላይ አስቀመጥነው።

በገነት ያሉ አትሮነሶችና አግዳሚዎች አስገራሚዎች ናቸው! በምድር ላይ እንዳሉት አይደለም አሠራራቸው። አግዳሚዎቹ እንደ ጥልፍ(ፈትል) ነበሩ፥ በተለያዩ የከበሩ ድንጋዮች የተሠሩ ነበሩ። አንዳንዶቹም ከአልማዝ የተሠሩ ነበሩ፥ ሌሎቹ ደግሞ ንጹህ እንቁዎች፥ አንዳንዶቹ ከንጹህ ወርቅ፥ እናም አንዳንዶቹ ደግሞ ከተለያዩ ድንጋዮች ድብልቅ የተሠሩ ነበሩ። ከዚያም **እግዚአብሔር** የሁሉም ነገር ባለቤት እንደሆነ ተረዳሁ፥ ልክ እንደተጻፈው በ[ሐጌ 2፡8] “*ወርቁ የእኔ ነው፥ ብሩም የእኔ ነው።*” **እግዚአብሔር** ፍጹም ሀብታም እንደሆነና በዓለም ያሉት ሀብታት ሁሉ የ**እርሱ** እንደሆኑ ተረዳሁ። እንዲሁም በተጨማሪ ዓለም በሙላቷ ሁሉ ለ**እግዚአብሔር** እንደሆነች፥ እናም በእምነት ለሚጠይቁት ሁሉ ሊሰጣቸው እንደሚወድ ተረዳሁ።

**ጌታም** አለ፡ “*ለምነኝ፥ አሕዛብን ለርስትህ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ እሰጥሃለሁ።*”([መዝሙር 2፡8]) ይህ በአግዳሚው ላይ ያስቀመጥነው መጽሐፍ በጣም ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ አንዱን ገጽ ለመግለጥ ወደ ሌላኛው የመጽሐፉ አቅጣጫ ይዘነው መሄድ ነበረብን። ጌታ እንደጠየቀን፥ መጽሐፉ ውስጥ ያለው ምን እንደሆነ ማንበብ ጀመርን። በመጀመሪያ፥ እኛ በማናውቀው እንግዳ ቋንቋ ስለተጻፈ ለማንበብ አስቸጋሪ ነበር። በምድር ላይ ካለው ማንኛውም ቋንቋ የተለየ ነበር፤ ሙሉ በሙሉ ሰማያዊ የሆነ ነገር ነበር። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ፥ የመረዳት ጸጋው ተሰጠን። ልክ ከዓይናችን ላይ ቅርፊቱ እንደተነሳልን ዓይነት ነበር እናም ከዛ ጽሑፉን መረዳት ቻልን፤ እንደ ራሳችን ቋንቋ በግልጽ።

የሰባታችንም ስም በመጽሐፉ ውስጥ እንደተጻፈ ማየት ቻልን። **ጌታም** የሕይወት መጽሐፍ መሆኑን ነገረን። ([ራእይ 3፡5]) የተጻፉት ስሞች በምድር ላይ የምንጠራባቸው ስሞች እንዳልሆኑ ተረዳን፤ እነዚህ ስሞች አዲስ ናቸው፥ ምክንያቱም ከተቀበለው በቀር ማንም የማያውቀው አዲስ ስም ይሰጠናል የሚለው **የእግዚአብሔር ቃል** ይፈጸም ዘንድ። ([ራእይ 2፡17])

በገነት፥ ስማችንን መናገር ችለን ነበር፥ ነገር ግን **ጌታ** ወደ ምድር መልሶ ካመጣን በኋላ እነዚያ ስሞች ከህሊናችንም ከልባችንም ተወስደው ነበር። **የእግዚአብሔር ቃል** ዘላለማዊ ነው፥ እናም ሊፈጸም ይገባዋል። ወዳጆቼ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፥([ራእይ 3፡11]) ማንም አክሊልህን አይውሰድብህ፥ **አብ** የሰጠህን ቦታ ማንም እንዳያስለቅቅህ ወይም እንዳያስተውህ ይላል። በገነት፥ አስገራሚ የሆኑ ሚሊየኖች ነገሮች አሉ፥ በአፋችን ግን ልንገልጻቸው አንችልም። ነገር ግን የሆነ ነገር ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፥ “***እግዚአብሔር** እየጠበቃችሁ ነው!*” ሆኖም ግን እስከመጨረሻ የሚጸኑት ሰዎች ብቻ ናቸው የሚድኑት! ([**የጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ** ወንጌል በማርቆስ 13፡13])

---

## --- (2[ኛ] ምስክርነት፥ ኤርኤል) ---

ወደ መንግሥተ ሰማያት መውጣት ስንጀምር፥ ብርቅዬ በሮች ወዳሉበት የሚያምር ቦታ ደረስን። ከበሮቹ ፊት ለፊት ሁለት መላእክት ነበሩ። መናገር ጀመሩ፥ ነገር ግን ቋንቋቸው መልአካዊ ስለነበር የሚሉትን ነገር ልንረዳቸው አልቻልንም። ነገር ግን **መንፈስ ቅዱስ** መረዳቱን ሰጠን። አቀባበል እያደረጉልን ነበር። **ጌታ ኢየሱስ** እጁን በበሮቹ ላይ አደረገና ተከፈቱ። **ኢየሱስ** ከእኛ ጋር ባይሆን ኖሮ፥ ፈጽሞ ወደ ገነት ውስጥ መምጣት ባልቻልን ነበር።

በገነት ያለውን ነገር ሁሉ ማድነቅ ጀመርን። ግዙፍ ዛፍ አየን፥ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ዛፍ "*የሕይወት ዛፍ*" ብሎ ይገልጸዋል።(ራእይ 2፡7) ወደ ወንዝ ሄድንና በውስጡ ብዙ ዓሦችን አየን። ሁሉም ነገር የሚያስገርም ነበርና እኔና ጓደኞቼ ውኃው ውስጥ ልንገባ ወሰንን። ከውኃው ስር መዋኘት ጀመርን። ዓሣዎቹ በዙሪያችን ሲንቀሳቀሱና ሰውነታችንን ሲዳስሱ አየናቸው። በምድር ላይ በተለምዶ እንደሚሆነው ሸሽተው አልዋኙም፤



**የጌታ** ህልውና አረጋግቷቸዋል። ዓሣዎቹ እንደማንጎዳቸው ስላወቁ አምነውናል። እግዚአብሔር በጣም ባርኮኛል እናም ተደንቄያለሁ በመሆኑም አንዱን ዓሣ ያዤ ከውኃው አወጣሁት። በጣም የሚገርመው ነገር ዓሣው በእጄ ውስጥ እንኳን ሆኖ በ**ጌታ** ህልውና እየተደሰተ ነበረ። ዓሣውን መልሼ ውኃ ውስጥ ከተትኩት።

በገነት ውስጥ በርቀት ነጫጭ ፈረሶች ማየት ችዬ ነበር፥ ልክ በ**እግዚአብሔር ቃል** ውስጥ እንደተጻፈው ራእይ 19፡11 "*ሰማይም ተከፍቶ አየሁ፥ እነሆም አምባላይ ፈረስ፥ የተቀመጠበትም የታመነና እውነተኛ ይባላል፥ በጽድቅም ይፈርዳል ይዋጋልም።*" እነዚያ ፈረሶች **ጌታ** ሕዝቦቹን፥ ቤተክርስቲያኑን ለመውሰድ ወደ ምድር ሲመጣ የሚጠቀምባቸው ናቸው። ወደ ፈረሶቹ ተጠጋሁና መታ መታ አደረኳቸው። **ጌታም** ተከተለኝና አንዱን እንድጋልብ ፈቀደልኝ።

መጋለብ ስጀምር፥በምድር ተሰምቶኝ የማላውቀው የሆነ ነገር ተሰማኝ። አንድ ሰው በዚያ ውብ ቦታ ሊያገኘው የሚችለውን ሰላሙን፥ ነፃነቱን፥ ፍቅሩን መለማመድ ጀመርሁ። ዓይኔ በሚያየው ነገር ሁሉ መደሰት ጀመርሁ። በዛ ውብ ገነት ውስጥ **ጌታ** ያዘጋጀልንን ነገር ሁሉ ልደሰትበት ፈለግሁ።



እንዲሁም የሠርጉን የግብዣ ጠረጴዛ ማየት ቻልን፥ ሁሉም ነገር ቀርቧል። መጀመሪያም ሆነ መጨረሻ የለውም። ለእኛ የተዘጋጁትን ወንበሮች አየን። እንዲሁም ለእኛ የተዘጋጁ የዘላለም ሕይወት አክሊሎችም ነበሩ። የተዘጋጁ ጣፋጭ ምግቦችን አየን፥ ወደ በጉ ሠርግ ለተጋበዙ ሁሉ።

መላእክት **ጌታ** ለእኛ እያዘጋጃቸው ላሉት ልብሶች ነጫጭ ልብሶችን ይዘው በዚያ ነበሩ። እነዚህን ሁሉ ነገሮች እያየሁ ተገርሜ ነበር። **የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔርን መንግሥት** እንደ ሕፃናት እንድንቀበላት ይነግረናል። (የጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በማቴዎስ 18፡3) በገነት ሳለን ልክ እንደ ሕፃናት ነበርን። በዚያ ባለው ነገር ሁሉ መደሰት ጀመርን፤ አበቦቹ፣ ነዋሪዎቹ… **ጌታ** ወደ ነዋሪዎቹ መካከል እንኳን እንድንሄድ ፈቅዶልናል።

ከዛም **እግዚአብሔር** ብዙ ሕፃናት ወዳሉበት ቦታ ወሰደን። **ጌታም** በመካከላቸው ነበረና ከእነርሱ ጋር መጫወት ጀመረ። ከእያንዳንዱ ጋር በቂ ጊዜ ለማሳለፉ እርግጠኛ ሆነ እናም ከእነርሱ ጋር በመሆኑ ተደሰተ። ወደ **ጌታም** ተጠግተን ጠየቅነው "***ጌታ** ሆይ፥እነዚህ ልጆች በምድር ላይ ወደፊት የሚወለዱ ናቸው?*" **ጌታም**፡ "*አይደለም፥ እነዚህ ልጆች በምድር ላይ የጨነገፉ (በውርጃ) ልጆች ናቸው።*" ብሎ መለሰልን። ይህን ስሰማ፥ በውስጤ የሚያንቀጠቅጥ ነገር ተሰማኝ።

በፊት ያደረግሁትን ነገር አስታወስሁ፥ **ጌታን** ሳላውቀው በፊት። በዚያ ሠዓት፥ ከአንድ ሴት ጋር በጓደኝነት ነበርንና አረገዘች። እንደጸነሰች ስትነግረኝ፥ምን ማድረግ እንደነበረብኝ አላወቅሁም ስለዚህ ውሳኔ ለመወሰን ጥቂት ጊዜ እንድትሰጠኝ ጠየቅኋት። ጊዜያት አለፉ እናም ውሳኔዬን ልነግራት ስሄድ፥ ረፍዶ ነበር ምክንያቱም ቀድማ ልጁን አስወርዳው ነበር። ያ በህይወቴ ላይ ጠባሳ አደረገ። **ጌታን** ወደ ልቤ ከተቀበልሁት በኋላ እንኳን፥ ያ ውርጃ ራሴን ይቅር ልልበት የማልችለው ነገር ነበር። ነገር ግን በዚያ ቀን **እግዚአብሔር** የሆነ ነገር አደረገ፥ ወደዚያ ቦታ እንድገባ አድርጎ እንዲህ አለኝ፥ "***ኤርኤል፥ እዛ ጋር ያለችውን ትንሽ ልጅ ታያታለህ? ያቺ ልጅ ያንተ ልጅ ናት።***" ያንን ሲነግረኝ፥ ልጅቷን አየኋት፥ ህመሜ፥ ለረዥም ጊዜ በነፍሴ ውስጥ የነበረው፥ መፈወስ ሲጀምር ተሰማኝ። **ጌታ** ወደ እርሷ እንድቀርብ ፈቀደልኝ እና እርሷም ወደ እኔ

ተጠጋች። በእጇ ይገፔ ዓይኖቿን ተመለከትሁ። ከከንፈሮቿ አንድ ቃል ሰማሁ፥ "*አባዬ!*" **የእግዚአብሔር** ምህረት በእኔ ላይ እንደሆነና ይቅር እንዳለኝ ተሰማኝ፥ነገር ግን ራሴን ይቅር ማለት መማር ይኖርብኛል።

ውድ ወዳጆቼ፥ ይህንን ጽሑፍ የምታነቡ፥አንድ ነገር ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። **እግዚአብሔር** ኃጢአታችሁን ይቅር ብሏችኋል፥ አሁን ራሳችሁን ይቅር ማለት መማር አለባችሁ። ይህን ምስክርነት ከእናንተ ጋር እንድካፈል ስለረዳኝ **እግዚአብሔርን** አመሰግነዋለሁ። ***ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ*** *ሆይ፥ ክብርና ውዳሴን ላንተ ሰጣለሁ!* ይህ ምስክርነት ከ**ጌታ** ነው፥**እርሱ** ይህን ራእይ እንድንቀበል ፈቀደልን። ይህን ምስክርነት የሚያነቡ ወንድሞች ሁሉ የዚህን ምስክርነት በረከት እንዲቀበሉና ሌሎችን ለማባረክ እንደሚጠቀሙበት ተስፋ አደርጋለሁ።

**እግዚአብሔር** ይባርካችሁ።

---

# --- (3ኛ ምስክርነት) ---

(*ራእይ 21:4*)

*እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ።*



ስንደርስ፥ እነዚህ ትላልቅ በሮች ተከፈቱልን፥ እናም በአበቦች የተሞላ መስክ ማየት ጀመርሁ። አበባዎቹ የሚያማምሩ ነበሩ እናም ደግሞ መዓዛቸው ልዩ ነበረ። ወደ ውስጥ መግባት ጀመርን እናም በምድር ላይ ተሰምቶን የማያውቅ ዓይነት ነፃነት ተሰማን። ልባችንን የሚሞላ ሰላም ተሰማን እናም አበባዎቹን እየተመለከትን ሳለን ልዩ አበባዎች መሆናቸውን አስተዋልን፤ እያንዳንዱ አበባ የተለዩ፥ እውነተኛ እናም ልዩ ቀለም ነበረው።

በልቤ ውስጥ፥ ለ**ጌታ** እንደነዚህ ዓይነት አበቦች ሊኖረኝ እፈልጋለሁ አልሁት። **ጌታ**ም የመስማማት ስሜት አሳየ። ወደ አበባው ተጠጋሁና መሳብ ጀመርሁ። ነገር ግን ምንም አልሆነም፥አበባውን መንቀል አልቻልሁም። ቅጠሎቹንም ሆነ አበባውን መቅጠፍ አልቻልሁም። እናም **ጌታ** ዝምታውን ሰበረና እንዲህ አለኝ፥ "***እዚህ ሁሉም ነገር መደረግ ያለበት በፍቅር ነው።***" በነካው ጊዜ አበባው ራሱን ለ**ጌታ** እጅ ሰጠ። ከዛም **እርሱ** ለእኛ ሰጠን። ጉዟችንን ቀጠልን እናም የአበባዎቹ ሽታ አሁንም ከእኛ ጋር ነበረ።

የሚያማምሩ በሮች ያለበት ስፍራ ደረስን። እነዚህ በሮች ተራ አይደሉም፥ በአሠራራቸው ያሸበረቁና የከበሩ ድንጋዮች ተሰካክተውባቸው ነበር። በሮቹ ተከፈቱና ብዙ ሰዎች ያሉበት ክፍል ውስጥ ገባን። ሁሉም ሰው ወደዚና ወደዚያ እየተሯሯጠና እያዘገጀ ነበር። አንዳንዶቹ የተጠቀለሉ አንጸባራቂ ነጫጭ ልብሶች በትከሻቸው ተሸክመው ነበር፥ ሌሎቹ ወርቃማ የክር ጥቅልሎችን ይዘዋል፥ እናም ሌሎች ደግሞ ውስጣቸው ጋሻ የሚመስል ሳህኖች ይዘዋል። ሁሉም በታታሪነት ይሯሯጥ ነበር።

**ጌታ**ን ይሄ ሁሉ ጥረትና ችኮላ ለምን እንደሆነ ጠየቅነው። ከዛ **ጌታ** አንድን ወጣት እንዲመጣ አዘዘው። ይህ ሰው የልብስ ጥቅልል በትከሻዎቹ ተሸክሟል። መጥቶም **ጌታ**ን በማደግደግ ተመለከተው። **ጌታ**ም ያንን የልብስ ጥቅልል ለምን እንደተሸከመ ሲጠይቀው፥ **ጌታ**ን ተመለከተና እንዲህ አለ፥ "***ጌታ*** *ሆይ፥ እነዚህ ልብሶች ለምን እንደሆኑ አንተ ታውቃህ! እነዚህ ልብሶች ለዳኑት ናቸው፥ የታላቋ ሙሽራ ልብስ!*" ይህን ስንሰማ ታላቅ ደስታና ሰላም ተሰማን። *ራእይ 19፡8* ሲነግረን "*የጌጠና የተጣራ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ እንድትጎናጸፍ ተሰጥቶአታል። ቀጭኑ የተልባ እግር የቅዱሳን ጽድቅ ሥራ ነውና።*"

ከዛ ቦታ ስንወጣ የበለጠ ብዙ ሰላም ተሰማን፥ ምክንያቱም **ጌታ ራሱ** ለእኛ መልካም ነገርን ሲያደርግልን ማየት ስለሚያስደስት ነው። **እርሱ** ለእናንተ ቦታም ጊዜም አለው ምክንያቱ ደግሞ እናንተ ለ**እርሱ** ጠቃሚ

(ልዩ) ናችሁ። ከዚያ ቦታ ስንወጣ፥ ዓይኖቻችን በገነት ውስጥ ባሉት እያንዳንዱ ጥልቅ ነገር ተዋጠ። እያንዳንዱ ነገር በራሱ ህይወት ያለው ነው የሚመስለው፥እናም በዚያ ያለው እያንዳንዱ እቃ ለ**እግዚአብሔር** ክብር ይሰጥ ነበር።



ከዚያም በሁሉም ዓይነት እድሜ የሚገኙ ሚሊየኖችና ሚሊየኖች ልጆች ያሉበት ቦታ ደረስን። ልክ **ጌታን** እንዳዩት፥ ሁሉም ሊያቅፉት ፈለጉ፥ ተጨማሪ ፍቅሩን ለማጣጣም፥ ምክንያቱም **እርሱ** ጥልቅ ፍቅራቸው (passion) ነውና። **ኢየሱስ** በዚያ ያሉት ልጆች ሁሉ ጥልቅ ፍቅር ነው። **ጌታ** ልጆቹን እንዴት እንደሚሳሳላቸው፥ እንደሚስማቸውና እጃቸውን እንደሚይዛቸው ስናይ እንደማልቀስ ተሰማን።

*መላእክት* ወደ **ጌታ** ቀርበው በተልባ እግር ልብስ የተጠቀለሉ ሕፃናትን ወደ **እርሱ** ሲያመጡ አየን። **ጌታም** ተንከባከባቸው፥ ዳሰሳቸው፥ እናም ግንባራቸውን ሳማቸውና *መላእክቱ* ይዘዋቸው ተመልሰው ሄዱ። **ጌታን** ለምን ብዙ ሕፃናት በዚያ እንዳሉ ጠየቅነው፥እነዚያ ሕፃናት ወደ ምድር ይላኩ እንደሆነ። **ጌታ** ለአፍታ ያህል ተሰማውና እንዲህ አለ፥ "***አይደለም፥ እነዚህ ወደ ምድር አይላኩም! እነዚህ በምድር ላይ የተጨነገፉ ናቸው፥ እነዚያ ወላጆች አይፈልጓቸውም። እነዚህ የእኔ ልጆች ናቸው እናም እኔ እወዳቸዋለሁ።***" ራሴን ነቀነቅሁ፥እናም ድምጼ ራሱ **ጌታን** እንደዚህ ዓይነት ጥያቄ ለመጠየቅ ተርበተበተ።

**ጌታን** ሳላውቀው በፊት፥እርሱ እውነተኛ ሕይወት መሆኑን ሳላውቅ በፊት፥እንደማንኛውም ሰው ስህተትንና ኃጢአትን ሰርቻለሁ። ከእነዚያ ኃጢአቶች አንዱ ያደረግሁት ውርጃ ነበር። ከ**ጌታ** ጋር ፊት ለፊት ሆኜ የጠየቅሁበት ጊዜ ነበር፥ "*ጌታ ሆይ፥ ከረዥም ጊዜ በፊት ያስወረድሁት ልጅ እዚህ ነው?*" **ጌታም** መለሰ "***አዎ።***" ወደ አንዱ ጠርዝ ሄድሁና ቆንጆዬ ትንሽ ልጅ አየሁ። ከእግሩ አጠገብ *መልአክ* ቆሟል። *መልአኩ* **ጌታን** እየተመለከተ ነበር፥እናም ልጁ ጀርባውን ለእኛ ሰጥቷል።

**ጌታም** አለኝ፥"***ተመልከቺ፥ያውና ልጅሽ።***" ላየው ፈለግሁ ስለዚህ ወደ እርሱ ሮጥሁ፥ነገር ግን *መልአኩ* በእጁ አስቆመኝ። መጀመሪያ ልጁ ምን እንደሚል ማዳመጥ እንዳለብኝ አሳየኝ። ትንሹ ልጅ የሚናገረውን ማዳመጥ ጀመርሁ። ወደ ሌላኛው ልጅ እያየና እየተናገረ ነበር። *መልአኩን* "*እናቴና አባቴ በቶሎ ይመጣሉ?*" ብሎ ጠየቀው። *መልአኩም*፥ ወደ እኔ ተመለከተና መለሰለት፥"*አዎን፥እናትህና አባትህ መምጫቸው ደርሷል።*"

እነዚህን ቃላት ለመስማት እድሉ ለምን እንደተሰጠኝ አላውቅም፥ ነገር ግን በልቤ ውስጥ ቃላቶቹ **ጌታ** የሚሰጠኝ ምርጡ ስጦታ እንደሆነ አወቅሁ። ይህ ሕፃን በቁጣ አልነበረም የሚናገረው፥ ወይም በህመም፥ ምናልባት እንዲወለድ እንዳላደረግነው እያወቀ ይሆናል። **እግዚአብሔር** በልቡ ባስቀመጠው ፍቅር ዝም ብሎ ይጠባበቃል።

*መሄዳችንን* ቀጠልን፥ ነገር ግን እኔ በልቤ የልጁን ምስል አስቀረሁ። በእያንዳንዱ ቀን፥ አንድ ቀን ከእርሱ ጋር ለመሆን ጥረት ማድረግ እንዳለብኝ አውቃለሁ። ወደዚያ ለመሄድ አንድ ተጨማሪ ምክንያት አለኝ፥ ምክንያቱም አንድ ሰው በ**መንግሥተ ሰማይ** ይጠብቀኛል። የ**እግዚአብሔር ቃል** ሲናገር በ[ኢሳይያስ 65፡19](#) "***እኔም በኢየሩሳሌም ሐሤት አደርጋለሁ በሕዝቤም ደስ ይለኛል፤ ከዚያም ወዲያ የልቅሶ ድምፅና የዋይታ ድምፅ አይሰማባትም።***"

ትናንሽ ተራራዎች ወዳሉበት ቦታ *መጣን*፥ እናም **ጌታ ኢየሱስ** እየዘመረ *መጣ*። ከፊት ለፊቱ ነጫጭ ልብሶችን የለበሱ ሰዎች በብዛት ነበሩ እናም በእጃቸው አረንጓዴ የወይራ ዝንጣፊዎች ይዘው ወደ ላይ ከፍ አደረጉት። በአየር ላይ ሲያወዛውዙት፥ ዘይቶችን ይረጭ ነበር። **እግዚአብሔር** ታላቅ ነገርን ለእናንተ አዘጋጅቶላችኋል! አሁን እናንተ ልባችሁን በፊቱ የምታደርጉበት ሠዓት ነው።

**እግዚአብሔር** ይባርካችሁ።

# --- (4ኛ ምስክርነት) ---

በመንግሥተ ሰማይ፥ በ**እግዚአብሔር ቃል** እንደተጻፈው ብዙ የሚያስገርሙ ነገሮችን አየን፥ [1ኛ ቆሮንቶስ 2፡9]
"*ነገር ግን። ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንደተጻፈ፥እንዲህ እንናገራለን።*"

መንግሥተ ሰማያት ስንደርስ ብዙ ነገሮችን ማየት እጅግ አስደናቂና አስገራም ነው፤ ብዙ ትላልቅ ነገሮች እናም የጌታን ክብር መሞላት። እጅግ ልዩ ነበረ፤ ብዙ ልጆች ያሉበት ቦታ። በዛ ቦታ ሚሊየኖች ልጆች እንዳሉ መናገር ይቻላል።

የተለያየ እድሜ ያላቸውን ልጆች አየን፥ ገነት በክፍል የተከፋፈለች ናት። እድሜያቸው ከ 2-4 የሚሆኑ ሕፃናት የሚኖሩበት የሕፃናት ቤቶችን አየን። እንዲሁም በ**መንሥተ ሰማይ** ያሉ ሕፃናት እንደሚያድጉና **የእግዚአብሔርን ቃል** የሚማሩባቸው ትምህርት ቤቶች እንዳሉ አስተዋልን። አስተማሪዎቹ መላእክት ናቸው እናም ልጆቹን የአምልኮ መዝሙሮችና **ጌታ ኢየሱስን** ማወደስ ያስተምሯቸዋል።

**ጌታ** ሲመጣ፥ **የንጉሣችንን** ታላቅ ደስታ ማየት ቻልን። ምንም እንኳን ፊቱን ማየት ባንችልም፥ ፈገግታውን ማየት እንችላለን፥ አካባቢውን በሙሉ ሞላው። **እርሱ** ሲደርስ ልጆቹ ሁሉ ወደ **እርሱ** ሮጡ! በእነዚያ ልጆች መሀል፥ ማርያም ትታየናለች፥ በምድር **የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ** እናት። የምታምር ሴት ነበረች። በዙፋን ላይ አልያም ማንም ሲያመልካት ወይም ሲያመሰግናት አላየንም። እርሷ ልክ በገነት እንዳሉት እንደሌሎች ሴቶች ነበረች፥ ልክ በምድር እንዳሉት ሌሎች ሰዎች መዳኗን ማሸነፍ ነበረባት። ነጭ ልብስና በወገቧ ላይ የወርቅ ቀበቶ ለብሳለች፥እናም ጸጉሯ ወገቧ ጋር ይደርሳል።

በምድር ላይ፥ ብዙ ሰዎች ማርያምን እንደ **ኢየሱስ** እናት ሲያመልኳት (ሲያወድሷት) እንሰማለን፥ ነገር ግን ልነግራችሁ የምፈልገው **የእግዚአብሔር ቃል**፥ "*ኢየሱስም። እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።*" ([የጌታችንና መድኃኒታችንኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በዮሐንስ 14፡6]) እንደሚል ነው። ብቸኛው የመንግስተ ሰማያት መግቢያ የናዝሬቱ **ኢየሱስ** ነው።

እንዲሁም ምንም ጨረቃም ሆነ ፀሐይ እንዳልነበሩ አስተውለናል። **የእግዚአብሔር ቃል** ሲነግረን [ራእይ 22፡5]
"*ከእንግዲህም ወዲህ ሌሊት አይሆንም፥ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ።*"

**የእግዚአብሔርን** ክብር ማየት እንችላለን። በሲያል ያየናቸውን ሰቅጣጭ ነገሮች ማብራራት ይከብደናል፥ነገር ግን ያየናቸውን ሰማያዊ ነገሮችንና የሠሪያችንን ፍጹምነት ማብራራት ደግሞ የባሰ ከባድ ነው። በዚያ በነበርንበት ጊዜ፥ መሮጥና ሁሉንም ነገር ማየት ፈለግን። በሣሩ ላይ እንተኛና **የእግዚአብሔርን** ክብር እናጣጥማለን። ያ ለስላሳው ፉጨት፤ ፊታችንን የሚዳብሰው ያ ለስላሳ ንፋስ፥ አስገራሚ የሆነ ነገር ነበረ።

በሰማይ መካከል፥ በንጹህ ወርቅ የተሠራ ግዙፍ መስቀል ማየት እንችላለን። ይህ ምንም ዓይነት የጣዖት አምልኮ (አይዶላትሪ፡ idolatry) ምልክት እንዳልሆነ እናምናለን ነገር ግን በመስቀል ላይ በሆነው **የኢየሱስ ክርስቶስ** ሞት በኩል እኛ ወደ **መንግሥተ ሰማይ** መግቢያ እንዳለን የሚያሳይ ምልክት ነው።

በገነት ጉዟችንን ቀጠልን። ከ**ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ** ጋር መራመድ አስደሳች ነው። ያኔ በእግጠኝነት የምናመልከው አምላክ ማን እንደሆነ ማወቅ እንችላለን፥ የምናመልከው **አምላክ** ማነው… የናዝሬቱ **ኢየሱስ**። በምድር ያለን አብዛኞቻችን በላይ **አምላክ** እንዳለ እናስባለን፥ ኃጢአት እስክንሠራ የሚጠብቅ፥ ሊቀጣንና ወደ ሲያል ሊልከን። ነገር ግን እውነታው ያ አይደለም። **ኢየሱስ** የፍቅር፥ የርኅራኄና የምህረት **አምላክ** ነው፤ በመዳን መንገድ እንድንቀጥል እጃችንን ይይዘናል።


**ጌታ ኢየሱስ** ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሰው እንድንገናኝ ፈቀደልን። ንጉሥ ዳዊትን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰውን ንጉሥ ዳዊት። መልከመልካም ሰው ነበረ፥ ረዥም እናም ፊቱ **የእግዚአብሔርን** ክብር ያንጸባርቅ ነበረ። በመንግሥተ ሰማይ በነበርንበት ጊዜ ሁሉ፥ ንጉሥ ዳዊት ሲያደርግ የነበረው ዝማሬ፣ ዝማሬ፣ ዝማሬ እናም ክብሩንና ውዳሴውን ሁሉ **ለእግዚአብሔር** መስጠት።

ይህን ምስክርነት ለሚያነቡ ሁሉ፥ ልነግራችሁ የምፈልገው **የእግዚአብሔር ቃል** ሲናገር ራእይ 21፡27 ”*ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር፥ ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኵሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም።*” እናም እኔ ልነግራችሁ የምፈልገው መንግሥተ ሰማያትን የሚወርሱት ጽኑኣን ብቻ እንደሆኑ ነው።

**እግዚአብሔር** ይባርካችሁ።

---

# --- (5ኛ ምስክርነት) ---



(2ኛ ቆሮንቶስ 5:10)
“*መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፥ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና።*”

በመንግሥተ ሰማያት፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረንን **አዲሲቷን ኢየሩሳሌምን** ማየት እንችላለን፥ የጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በዮሐንስ 14፡2 “*በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤*” ከተማዋን ማየትና መግባት እንችላለን፤ እወነተኛና አስገራሚ ከተማ ናት! **ኢየሱስ** እዚያ የሄደው እነዚህን መኖሪያ ስፍራዎች ሊያዘጋጅልን ነው።

በከተማዋ እያንዳንዱ መኖሪያ ወይም ቤት የባለቤቱ ስም በቤቱ ፊት ለፊት ተጽፎበታል። ይህች ከተማ ገና ማንም አይኖርባትም፥ ነገር ግን ለእኛ ተዘጋጅታለች። ወደ ቤቶቹ ውስጥ እንድንገባና ውስጥ ያሉትን ነገሮች እንድናይ ተፈቅዶልን ነበር። ነገር ግን በኋላ ላይ ከተማዋን ስንለቅ፥ ያየናቸውን ነገሮች ረሳናቸው፥ እነዚያ ትውስታዎች ከእኛ ተወስደውብን ነበር። ሆኖም ግን፥ የቤቶቹ ጉበኖች በውድ ብረቶች እንደተለበጡና ብዙ ዓይነት የከበሩ ድንጋዮች እንደተሰካኩባቸው ማስታወስ እንችላለን። እንዲሁም በውስጣቸው ንጹህ ወርቅ አለባቸው።

የዚህች ከተማ ወርቅ ልክ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚገልጸው ነው፤ ብርሃን አስተላላፊና አንጸባራቂ ነው። በምድር ያለው ወርቅ በገነት ያለውን ወርቅ አንጸባራቂነትም ሆነ ውበት አይወዳደረውም።
ከዚህ በኋላ፥ ብዙ ማጠራቀሚያዎች ወዳሉበት ቦታ ደረስን። በነዚያ ማጠራቀሚያዎች ውስጥ ኩልል ያሉ እንባዎች ነበሩባቸው። እነዚያም በምድር ላይ የፈሰሱ የእግዚአብሔር ልጆች እንባዎች ናቸው። የማማረር እንባዎች አልነበሩም፥ ነገር ግን ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ሆነው ያነቧቸው፤ የንስሐ እንባዎች፥ የምስጋና እንባዎች ነበሩ። **እግዚአብሔር** እነዚህን እንባዎች በገነት እንደ ውድ ማዕድናት አስቀምጧቸዋል፥ ልክ እንደ ተገለጸው በመዝሙር 55(56) ፡8፥ “*አምላክ ሆይ፥ ሕይወቴን ነገርሁህ፤ እንባዬን እንደ ትእዛዝህ በፊትህ አኖርህ።*”

እንዲሁም በጣም ብዙ *መላእክት* ወደ ነበሩበት ቦታ መጣን። በገነት ውስጥ ብዙ ዓይነት *መላእክትን* ማየት ብንችልም፥ ይህ ስፍራ ግን አንድ ልዩ የሆኑ የመላእክት ዓይነት ብቻ ነበረው። **ኢየሱስ** ለእያንዳንዱ ሰው አንድ ልዩ *መልአክ* እንዳለው አየን። እንዲሁም መልአኩ በመላ ዘመናችን ሁሉ አብሮን እንደሚሆን አሳየን።

ጌታችን መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ከተመደበው *መልአክ* ጋር አስተዋወቀን። ባሕሪያቶቻቸውን ማየት ቻልን፥ነገር ግን **እግዚአብሔር** እነዚህን ነገሮች ለሌሎች እንዳንገልጥ ነገረን። በመዝሙር 90(91) ፥11 "*በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና፤*" የሚል እናነባለን።

ብዙ ባለ ቁልፍ ማስቀመጫዎች ወዳሉበት ቦታ ደረስን፥በውስጣቸው ብዙ ዓይነት አበቦች አሉ። አንዳንዶቹ አበባዎች ክፍት፥የሚያምሩና የሚያንጸባርቁ ነበሩ። ነገር ግን አንዳንዶቹ ያቀረቀሩ ነበሩ፥እናም አንዳንዶቹ የባሰ ጠውልገዋል። **ኢየሱስን** የእነዚህ አበቦች ትርጉም ምን እንደሆነ ጠየቅነው። **እርሱም** መለሰለን "*ምክንያቱ የእያንዳንዳችሁ ህይወት ከእነዚህ አበባዎች እንደ አንዱ ስለሆነ ነው።*" አንዱን አንጸባራቂ አበባ አነሳና እንዲህ አለ፥"*ይህ አበባ ከእኔ ጋር ያላችሁን የግንኙነት (የትስስር) ሁኔታ ያስረዳል።*" ያን አበባ ተወና ያቀረቀረውን ሌላውን አንድ አበባ አነሳ። እንዲህም አለን፥"*ተመልከቱ፥ይህ ሰው ያቀረቀረው ፈተና ወይም አስቸጋሪ ሁኔታ ስላጋጠመው ነው። በዚህ ህይወት ውስጥ ከእኔ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያጨናግፍ የሆነ ነገር አለ። እነዚህ አበቦች ሲያቀረቅሩ ደግመው እንዲያንጸባርቁና ጤነኛ እንዲሆኑ ምን እንደማደርግ ማወቅ ትፈልጋላችሁ?*" ከዛም አበባውን በእጁ ያዘና እንዲህ አለ፥"*እንባዬን በላያቸው አፈሳለሁ ቀናም አደርጋቸዋለሁ።*" ይህ አበባ በኃይለኛ ሁኔታ እንዴት እንደገና ሕይወት ማግኘትና ቀና ማለት እንደጀመረ እንዲሁም ቀለሞቹ በድጋሚ ሲወጡ አየን።

ከዛም አንዱን የጠወለገ አበባ አንሳና ወደ እሳት ውስጥ ወርውሮት እንዲህ አለ፥ "*ተመልከቱ፥ ይህ ሰው ያውቀኝ ነበር እናም ከእኔ ፈቀቅ ብሎ ሄደ። አሁን ያለ እኔ ሞተ እናም ወደ እሳት ውስጥ ተጣለ።*" (የጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በዮሐንስ 15፥5-6)

ያንን ቦታ ለቀን ስንሄድ፥ በርቀት የሚያምር ቤተ-መንግሥት አየን። ማንም ወደዚያ ቤተ-መንግሥት ለመቅረብ አልቃጣም፥ እናም ያ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያወራለት መሆኑን አመንን በራእይ 22፥1 " *በአደባባይዋም መካከል ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚወጣውን እንደ ብርሌ የሚያንጸባርቀውን የሕይወትን ውኃ ወንዝ አሳየኝ።*" ቤተ-መንግሥቱ ምን አልባት በእግዚአብሔር ዙፋንና ህልውና አጠገብ እንዳለ አመንን።

እነዚህን ሁሉ በመንግሥተ ሰማያት እየተለማመድን ሳለ፥በልባችን ውስጥ በጣም ብዙ ደስታ ነበረ፥መረዳትን ሁሉ የሚልቅ ሰላም ነበረን። (ፊልጵስዩስ 4፥7) ልክ እንደተጻፈው ተረዳነው በ1ኛ ጴጥሮስ 1፥4 "*...ይህም ርስት በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል።*"

---

# --- (6ኛ ምስክርነት) ---

(የጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በሉቃስ 22፥29-30)

"*አባቴ እኔን እንደ ሾመኝ እኔ ደግሞ በመንግሥቴ ከማዕዴ ትበሉና ትጠጡ ዘንድ፥ በአሥራ ሁለቱ በእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በዙፋኖች ትቀመጡ ዘንድ ለመንግሥት እሾማችኋለሁ።*"



በዚያ አስደናቂ ቦታ፥**እግዚአብሔር** በመላው ዓለም ሊገኝ ይችላል ብለን የማናስበውን በጣም የሚያምር የእንግዳ መቀበያ አዳራሽ አሳየን። በንጹህ ወርቅና በምድር ላይ በማይገኙ እንቁዎች የተሠሩ ሁለት ወንበሮች ያሉበት አንድ ግዙፍ ዙፋን አየን። በዙፋኑ ፊት ለፊት መጨረሻ የሌለው ጠረጴዛ ነበር፥በላዩም ላይ ነጭ የጠረጴዛ ልብስ አለ። በጣም ነጭ ከመሆኑ የተነሳ በምድር ላይ ካለ ከምንም ነገር ጋር ልናወዳድረው እንችልም።

ሁሉም ዓይነት የሚያስጎመጁና የሚጣፍጡ ምግቦች በጠረጴዛው ላይ ነበሩ። ብርትኳን የሚያህሉ ወይኖች አየን፥እናም **ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ** አንዳንዶቹን እንድንቀምስ ፈቀደልን። እስካሁን ጣዕማቸውን ማስታወስ

እንችላለን፥ በጣም አስገራሚ የሆነ ነገር ነበር! ወንድሞቼና ወዳጆቼ፥ በመንግሥተ ሰማያት ያሉትንና **እግዚአብሔር** ለእኛ ያዘጋጃቸውን ነገሮች ልትገምቷቸው አትችሉም። (1ኛ ቆሮንቶስ 2፥9)

እንዲሁም በጠረጴዛው ላይ፥ **እግዚብሔር** ዳቦውን፥ "መናውን" እንድናይ ፈቀደለን። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እርሱ ይነግረን የነበረው የ**እግዚአብሔር** ዳቦ ይህ ነበረ። በምድር ላይ በጭራሽ የማይገኙ አስገራሚ ነገሮችን ጨምሮ ጣዕሙን እንድናጣጥም ተፈቅዶልን ነበር።

እነዚህ ነገሮች በመንግሥተ ሰማያት የሚጠብቁን የማይበላሹ ውርሶቻችን ናቸው። መንግሥተ ሰማያትን ስንወርስ አንዳንድ አስደናቂ የሚያስጎመጁና ጣፋጭ ምግቦችን እናጣጥማለን። ወንበሮቹ በሁለቱም የተረጴዛው ጎን መሆናቸው አስደነቀን። እነዚህ የተዋቡ ወንበሮች በእያንዳንዳቸው ላይ ስሞች ተጽፈውባቸዋል። በነዚያ ወንበሮች ላይ ስሞቻችንን በግልጽ ማንበብ እንችል ነበር፥ ነገር ግን ስሞቻችን እዚህ ምድር እንደምንጠራባቸው ዓይነት አይደሉም። ከእኛ በቀር ማንም ያማያውቃቸው አዲሶቹ ስሞች ነበሩ። (ራእይ 2፥17)

**በእግዚአብሔር ቃል** ተጽፎ የነበረው አስገረመን፥ "*ነገር ግን መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፥ ስማችሁ ግን በሰማያት ሰለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ።*" (የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በሉቃስ 10፥20) በዚያ ብዙ ወንበሮች ነበሩ! ወደ መንግሥተ ሰማያት መምጣት ለሚፈልግ ሁሉ በቂ ቦታ አለ። እንዲሁም ደግሞ ከጠረጴዛውም የተወሰዱ ወንበሮችም ነበሩ። ያም ማለት **እግዚአብሔርን** ማገልገል የታከታቸው፥ እናም ስማቸው ከሕይወት መጽሐፍ የተደመሰሰ እናም ከበጉ **ሠርግ እራት** የተባረሩ(የተለዩ) ወንዶችና ሴቶች አሉ ማለት ነው።

እንዲሁም **እግዚአብሔር** ከመጸሐፍ ቅዱስ ሰዎችን እንድናይ ፈቀደልን፥ በጥቅሶች ውስጥ ስለ እነርሱ ያነበብንላቸው አስገራሚ ቅዱሳን። አብርሃምን በማየታችን ተደነቅን። አብርሃም ሽማግሌ ነበር፥ ነገር ግን በሰውነቱ ወይም በአቋሙ አይደለም። ሽምግልናው በነበረው ጥበብ ነበር። የአብርሃም ጸጉር ሙሉ በሙሉ ነጭ ነበር፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ጸጉር እንደ ብርጭቆ ወይም እንደ አልማዝ ስባሪ ነበር። በጣም ያስገረመን ደግሞ እርሱ ከእኛ ወጣት መሆኑ ነው። በገነት፥ ሁላችንም እንታደስና ወጣቶች እንሆናለን። እንዲሁም በንግግሮቹ ተገርመን ነበር። አብርሃም አንድ መቼም የማንረሳው ነገር ነገረን። ወደ መንግሥተ ሰማያት መልካም አቀባበል አደረገልንና በቅርቡ በዚህ ቦታ እንደምንሆን ነገረን፥ ምክንያቱም **የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ** መምጫ በፍጥነት እየቀረበ ነው።

**በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።**

ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu Abdissa, matoughen@gmail.com